# ይቅር ማለት ሌላ፣ መርሳት ሌላ።

**ደጃት ካሳ**

**09/07/2007**

*የቅንጅት ኣመራሮች በሽማግሌዎች ጥረት ከእስር ከተፈቱ ወዲህ በ"መንፈሱ" ተከታዮች ዘንድ ሰርግና ምላሽም እብደትም እያየን ነው። የመንፈሱ መሪዎች ደግሞ በምእራቡ ዓለም የእተዘዋወሩ የሚያደርጉት "ትግል" ጀምሯል። ይለያል ዘንድሮ! እኛም መለስ ብለን ስለነሱ ለመፃፍ ፈለግን። እንዳይረሳ ዘንድ። ይቅር ማለት ሌላ መርሳት ሌላ። በነሱም ዘንድ እንደዚሁ ነው።*

## አ ን ድ

የኢትዮጵያ ቃላዊ ሃብት ነገሮችን በቀላሉ ለመግለፅና በኣጭሩ ለማስረዳት ያለው ፋይዳ የትየለሌ ነው። ለምሳሌ በ "ቅንጅት ለኣንድነትና ለዴሞክራሲ" ፓርቲ ውስጥ "መቀናጀት"፣ "ኣንድነት" እና "የዴሞክራሲ ባህል" ቢኖሩ "ስም ይመርሆ ለግብር" ወይም ደግሞ "ስምን መልኣክ ያወጣዋል" እንል ነበር። የፖለቲካን ስንክሳር በቀላሉ መገንዘብ ለሚቸግረው ሰው "ቅንጅት እኮ እንደ ስሙ ነው" ብንለው ስለፓርቲው በቀለሉ ኣጠቃላይ ኣወንታዊ ግንዛቤ ይኖረዋል። በተመሳሳይ መንገድ በ "ቅንጅት ለኣንድነትና ለዴሞክራሲ" ፓርቲ ውስጥ "መቀናጀት"፣ "ኣንድነት" እና "የዴሞክራሲ ባህል" ባይኖሩ "መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ" እንላለን። ኣሁንም የፖለቲካን ስንክሳር በቀላሉ መገንዘብ ለሚያዳግተው ሰው ይህንን ብሂል ስንነግረው ስለፓርቲው በቀለሉ ኣጠቃላይ ኣሉታዊ ግንዛቤ ይኖረዋል።

የዚህ ፅሁፍ ኣላማ በቅንጅት ለኣንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ውስጥ "መቀናጀት"፣ "ኣንድነት" እና "ዴሞክራሲ" እስከምን ያህል እንደሆኑ ማመላከትና፣ ቅንጅት በኢትዮጵያ የፖለቲካና የዴሞክራሲ ግንባት ትግል ኣቋምና ፋይዳ ለማሳየት መሞከር ነው። ኣንዳንድ ጊዜ "ኣገር ያወቀውን ፀሃይ የሞቀውን" እንደገና መልሰን መላልሰን እንድናነሳው እንገደዳለን። ምክንያቱም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ዲስኩር ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ በየጊዜው "ሀ" ብሎ መጀመር ወይም ደግሞ ያለፈውን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ መተው (መርሳት) የተለመዱ ኣካሄዶች ናቸው። ያለፈውን ትተን (ረስተን) "ኣዲስ" (ኣዲስ የሚመስለን) እንቅስቃሴ በጀመርን ቁጥር ብዙ የተራመድን ይመስለናል። የሚገርመው ግን ከብዙ ጊዜ በኋላ ጋት እንኳን መራመድ ኣቅቶን ባለንበት እንረግጣለን።

መጀመሪያ በቅንጅት ያለው "**መቀናጀትን**" እንመልከት። በኔ ኣመለካከት የኣንድን የፖለቲካ ፓርቲ ባህርይ ከመስራቾቹ ወይም መሪዎቹ የርእዮተ ዓለም፣ ባህል፣ የግል ወይም የቡዱን ታሪክና ፍላጎት እና ሌሎች እሴቶች ጋር የተቆራኘ ነው። በዚህ ረገድ ተመሳሳይነት የሌላቸው ፖለቲከኞች ኣንድ ፓርቲ መስርተው ማስኬድ ኣይችሉም። ለምሳሌ ኣቶ ሃይሉ ሻወልና ኣቶ ልደቱ ኣያሌው በኣንድ ወቅት የመላ ኣማራ ኣንድነት ድርጅት ኣባላት ነበሩ። ኣቶ ልደቱ ኢዴፓን ሲመሰርቱ ኣቶ ሃይሉ መላ ኣማራን መላ ኢትዮጵያ ኣድርጌዋለሁኝ ኣሉ። ሁላችን እንደምናውቀው በ1997 ኣም ምርጫ ዋዜማ ላይ ኣቶ ልደቱና ኣቶ ሃይሉ "ቅንጅት" ፈጠርን ኣሉ። ያን ያህል የዓላማና የርእዮተ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ዓለም አንድነት ከኖረ መጀመሪያውኑ ለምን ተለያዩ? ይህ ማን ያስታውሳል? እንረሳለን። መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅስ መች ይሆንልናል?

ቀስተ ደመና ውስጥ ያሉ አባላት (መስራቾች) በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ "አዳኝና ታዳኝ" ሆነው አናገኛቸዋለን። የሚያስተሳስራቸው ርእዮተ ኣለም፣ የፖለቲካ ባህል ወይም እሴት የላቸውም። ፕሮፌሰር መስፍን እና ዶ/ር ብርሃኑ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር ሰሌክቲቭ አምኔዥያ ነው። እርስ በርስ አውቀው ተረሳሱ፣ በነሱ ዘመን በዚች ኢትዮጵያችን የምንላት ምድር የተደረጉትን ግፎች ረሱ፤ እነዚያ ግፎች የፈፀሙትንም ረሱ። የየራሳቸው አሉታዊ አስተዋፅኦም ረሱ። ኢህአዴግ ዲያብሎስ መስሎ ታያቸው። ከዛ ማርና ወተት ሆኑ። ፓርቲም መሰረቱ። አርቲስት ደበበ እሸቱም ተካተቱ። ሻለቃ አድማሱ ገበየሁም ገቡ። የማያጠግብ እንጀራ...። ከዚያም አልፈው በደርግ ሚኒስቴር-ነበር የሚመራው መላ ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ ጋር ተቀናጁ።

ኢደፓ-መድህን የኢደፓና የመድህንን በስም ደረጃ እንኳን ላለማጣት የሚሄድ ነው። አንድነታቸውና ልዩነታቸው በኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች ካለው አንድነትና ልዩነት ጋር ተመሳሳይነት ይኑሮው አይኑሮው ኣላውቅም። የኛ ፓርቲ ህብረ ብሄራዊ ፓርቲ ነው ካሉ፣ ኢህአዴግን አይመስሉም። ኢህአዴግን የማይምስሉ ህብረ ብሄራዊ ከሆኑ ደግሞ ስማቸው እንደ ኢትዮ-ሱዳን ወይም ኢትዮ-ኬንያ ሆነ። ይህ መቀናጀት ወይም አንድ መሆን በኢደፓ-መድህን ውስጥም የሚቀረው ነገር እንዳለ በቂ ኣመላካች ይመስለኛል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያው ሊግ የቅንጅት አንድ መስራች አባል ነበር። የዚህ ፓርቲ ታሪክ ብዙም ባላውቀውም፤ የቆየ ፓርቲ እንደሆነ አውቃለሁ።

በዚህ አቋም የነበሩ የቅንጅት አባል ድርጅቶች በምርጫ 97 ዋዜማ ከኢህአዴግ ጋር ገመድ ለመጓተት ከተቀናጁ በኋላ ወደ አንድ ፓርቲነት መሸጋገር የማይሞከር ሆነባቸው። በምረጫ ማግስት መፈረካከስ ጀመሩ፤ መፈረካከሱ ማቆሚያ የትየለለ ሆነብን።

በመቀጠል በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ያለችዋ "አንድነት" እንመልከት። በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ውስጥ "አንድነት"ን ከፖለቲካዊ ፋይዳው ይልቅ ስሜት ኮርኳሪነቱ ይልቃል። በብሄረሰብ ደረጃ የተደራጀው ኢህአዴግ ለኢትዮጵያ አንድነት ከፍተኛ የአደጋ ምንጭ እንደሆነ በህዝብ ዘንድ ስሜት የመፍጠር የ15 ዓመት ፕሮፓጋንዳ ሰምተናል። የዚህ ፕሮፓጋንዳ አራማጆች የተለያዩ ካባዎች ለብሰው ሌተቀን ሲኳትኑም አይተናል። በቅንጅት ውስጥ ያለው "አንድነት" ትርጉም ወይም ፋይዳ የሚኖረው ኢህአዴግ የኢትዮጵያ አንድነት የአደጋ ምንጭ መሆኑን ስናምን ብቻ ነው። ይህንን እንደ መነሻ (Context) ካልወሰድን የቃሉ ፖለቲካዊ ሃይል ያን ያህል አይደለም። ኢህአዴግ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ለኢትዮጵያ አንድነት የቆመ መሆኑ ስንገነዘብ ደግሞ የቃሉ ፋይዳ ማወናበድ (መሸወድ) መሆኑን እናያለን።

ለነገሩማ አንድ አለመሆን አንገትዋ አሸዋ ውስጥ የቀበረችው ሰጎን እንምሰል ካልተባለ በስተቀር ድሮውም ያልነበረ መሆኑ የታወቀ ነው። ከምርጫ 97 በፊት ኢትዮጵያን ከኢህአዴግ አገዛዝ እንታደጋታለን የሚሉት ሺ ምንተሺ ተቀዋሚዎች እንደለመዱት ወደ ምዕራቡ ዓለም ተጉዘው ከደጋፊዎቻቸው ጋር ሲማከሩ "ተባበሩ አልያም ተሰባበሩ" በተባሉበት መሰረት የተቀላቀሉ እንጂ ህብረትና አንድነት ለመፍጠር ታሪካቸውና ባህሪያቸው የማይፈቅደው ነገር ነበር። አንዳንድ ዜጎች



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በየቀኑ እየተሰነጣጠቁ ነው ሲሉ ይደመጣሉ። እኔ የምለው ግን መች አንድ ሆነው ያውቁና ነው? ከኢህአዴግ ጋር ለስልጣን ገመድ ጉተታ ማበርና በፖለቲካ አመለካከትና በነጠረ ርእዮተ ዓለም መከተል ምክንያት ማበር የተራራቁ ናቸው።

ባንድ ማህበረሰብ ያሉ ልዩነቶች (ማናቸውም ዓይነት) አስወግዶ አንድ መሆን በንደፈ ሃሳብ ደረጃ ሊታሰብ ይችል ይሆናል። አንድ ቋንቋ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ባህል፣ ወዘተ። በተግባር ይህን እውን ለማድረግ ግን በማህበረሰቡ ያሉ የሚመለከታቸው ግለሰቦች (ቡዱኖች ሳይሆኑ) መቶ በመቶ መስማማት አለባቸው። ይህ ደግሞ የማይሆን ነው። በኢትዮጵያውያን ዘንድ ያሉ ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች የአንድነት አደጋዎች እንደሆኑ ከመመልከት የመነጨ የአንድነት አምር (ኮንሰፐት) ለመገንዘብ ያዳግተኛል። ልዩነትን የማይቀበል አንድነት?

በመቀናጀት ስር የዘረዘርኩዋቸው ተፃርሮዎች እዚህም ለማሳየት ልሞክር። በኢትዮጵያ ደረጃ ለአንድነት እታገላለሁ የሚል ፓርቲ መጀመሪያ በፓርቲ ደረጃ አንድነት ማረጋገጥ አለበት። አንድ ርእዮተ ዓለም፣ ስለኢትዮጵያ አንድነት አንድ ራእይ፣ ስለኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የእድገት አቅጣጫ አንድ አመለካከት መያዝ ያስፈልጋል። አንድ ቋንቋ መናገር፣ ተመሳሳይ ካሪኩለም ቪቴ መኖር፣ አብሮ ማኪያቶ መጠጣት፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስለተሰናበቱ ተመሳሳይ ብሶት መያዝ፣ ኢህአዴግን መጥላት፣ ወዘተ ከቶውንም የአንድነት ምልክት አይሆኑም። የደርግ፣ የመኢሶንና፣ የኢህአፓ ሰዎች አንድነት ፈጠርን ቢሉን፤ እሰየው ይሻላቸዋል ብለን የምናልፈው ነገር መሆን የለበትም። "ይህ እንዴት ይሆናል?" በሎ ማን ይጠይቃል። እንረሳለና።

ሰሞኑን አዲስ ፎርቹን አንድ ማለፊያ ፅሁፍ አስነብቦናል። An Opposition in Ideological Disarray የሚል። ርእዮተ ዓለማዊ አንድነት የሌላቸው መሆኑን አሳይቶናል። እንዲያውም የኢህአዴግ ርእዮት አራማጆች ሆነው ታዩ።

በመጨረሻ በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ያለችዋ "ዴሞክራሲ" የምትለዋ አምር (Concept) ለማየት እንሞክር። የዴሞክራሲ ዋናው ግብ የህዝብን መሰረታዊ ፍላጎት ማስጠበቅ ነው። ህዝብን የማይፈልገውንና የማይበጀውን እንዲያደርግ ማስገደድ ደግሞ ኢዴሞክራሲያዊ ተግባር ነው። ህዝብን የማይፈልገውንና የማይበጀውን እንዲያደርግ በሰይፍና በሽብር ማስገደድ ደግሞ የኢዴሞክራሲያዊ ተግባር ጣራ ነው። ደርግና ኢህአፓ በኢትዮጵያ ምድር ሽብርተኝነትን በህበረቀለማት አስውበው የፈለሰፉና ያራመዱ ናቸው። ሽብርተኝነትን ያራመዱትንና የተራመደባቸው ተቀናጅተው፣ በኢትዮጵያ የአንድነትና የዴሞክራሲ መና እናመጣለን ይሉናል። ባህሪያቸው እንኳን ተለውጧል ብንል፣ ተግባራቸው እንዴት ይለወጣል? ብቻ አንድ የማይለወጥ ነገር ስላለ እድለኞች ናቸው። የትናንትን ነገር የመርሳት ባህሪያችን አልተለወጠም። እንዲሁም የዴሞክራሲ ስርዓት ክፋቱ በአንድ ወቅት የለየላቸው ፀረ-ዴሞክራሲ የነበሩ ሃይላት እድል የማይነፍግ መሆኑ ነው።

ሚዛናዊ (Rational) አስተሳሰብ ያላቸው ዜጎች የቅንጅትን የአንድነትና የዴሞክራሲ ሰባኪነት ከመጀመሪያው ጥያቄ ውስጥ መክተት ነበረባቸው። አሁንም ሊታገሉት ይገባል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## ሁ ለ ት

ስለቅንጅት ባህሪይ ባጭሩ ይኸን ካልኩኝ፣ ቅንጅትን የመሰለ ድርጅት በኢትዮጵያ ፖለቲካ እንዴት የትግል ሜዳ ሊያገኝ እንደቻለ ለማመለከት ልሞክር። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ዲስኩር ተቀባይ (Audience) ማን ነው? ብለን መጠየቅና መልስ መሻት ቅንጅት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ውስጥ እንዴት ተዋናይ ሊሆን እንደሚችል ሊያሳየን ይችላል። ኦዴንሱ በሚከተሉት ቡድኖች ማስቀመጥ የሚቻል ይመስለኛል። (1) የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተራ አባላት፣ (2) የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ደጋፊዎች፣ (3) ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ያልወገነ የተማረ ህዝብ፣ እና (4) ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ያልወገነ ያልተማረ ህዝብ፤ ብለን ልንከፍለው እንችላለን።

በተራ ቁጥሮች (3) እና (4) የተመለከቱ ወገኖች ይህ ፅሁፍ የሚያተኩርባቸው አይደሉም። የፖለቲካ ተሳትፎኣቸው በምርጫ ወቅት ይሻላል ያሉትን ፓርቲ ከመምረጥ ያለፈ አይሆንም። በተራ ቁጥሮች (1) እና (2) ያሉ ግን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ተዋንያን አካል ናቸው። ባህሪያቸው መመልት ጠቃሚ ነው። በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ የፕረስ ውጤቶች (መፃህፍት፣ መፅሄቶች፣ ጋዜጦች፣ ደረገፆት፣ ብሎጎች) ስንመለከት ኢትዮጵያን ወደተሻለ የእድገትና የስልጣኔ ደረጃ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ የርእዮተ ዓለም ሃሳቦች፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች፣ የፖለቲካ የማህበራዊ ንሮ ኣቅጣጫዎች ፖለቲከኞች የመብዛታቸውን ያህል ኣናይም። በደጋፊነትና በኣባልነት የሚፈረጁትም የሚደግፉትን ፓርቲ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመርዳት ካላቸው ኣቅም ይልቅ ጠላት ከሚሉት ፓርቲ ጋር ገመድ ለመጓተት ብቻ የተዘጋጁ ናቸው። ለነገሩማ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ውስጥ በ1997 ምርጫ የዴሞክራሲ መሲሆች በመምሰል ብቅ ያሉት በኣካዳሚ ብቃታቸው በረዥም ዘንግ እንኳ የማይነኩቱ ምን ፃፉ? ምንስ ኣበረከቱ?

ኣቶ ልደቱና ዶ/ር ብርሃኑ ኣንዳንድ መፅሃፍ ፅፈዋል። በርግጥ ኣላነበብኩዋቸውም። መፅሃፎቹ ካነበቡ ሰዎች ጠይቄ እንደተረዳሁትና በመፅሃፎቹ ላይ የተሰጡ ኣስተያየቶች (በኢንተርኔት) እንደተረዳሁት ግን በምርጫ 97 ላይ ያተኮሩ እንጂ ኣዲስ የርእዮትና የፖሊሲ ኣቅጣጫ ኣመላካቾች ኣይመስሉኝም።

የኢህኣዴግ ኣባላትና ደጋፊዎች ኣብዮታዊ ዴሞክራሲን ኣቶ መለስ በሚፈልጉት ጥልቀትና ስፋት ይግባቸዋል ባልልም ከካድሬ በላይ ያሉቱ ሊያሰራ የሚችል እውቀት ኣላቸው ባይ ነኝ። የልማታዊ መንግስት ምንነትም መሰረታዊ ግንዛቤ የሚኖራቸው ይመስለኛል። ሆኖም ግን በኢህኣዴግ ልሳናት የሚታተሙ ፅሁፎች በኣባላትና በደጋፊዎችም ጥልቅ ሂስ ኣይሰጥባቸውም። ዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ኣለ። እንዲያውም ኣብዛኛዎቹ ዜና ኣዘል እንጂ የርእዮትና የፖሊሲ ጉዳዮች ኣይበዙባቸውም።

የዚህ ዓይነት ኣባልና ደጋፊ ጥቅሙ ብዛቱ ላይ እንጂ የፖለቲካ ብቃቱ ኣይደለም። ብቃት የሌለው በዙ ኣባልና ደጋፊ ደግሞ ኣልያም በማእበል እንደተመታ የውቅያኖስ ውሃ ሊሸሽ ይችላል። ኣንዳንዴም የምንወዳቸው ሰዎች በማንኛውም ምክንያት ከፓርቲው ሲሰናበቱ (በህመም፣ በሞት፣ በስራት፣ በግምገማ፣ በራስ ፈቃድ) የፓርቲው ደጋፊነታችን እንነፍጋለን። ኣስራ ኣንዱ የህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ ኣባላት ከፓርቲው ሲሰናበቱ (ሲባረሩ) ብዙ የህወሓት ኣባላትና ደጋፊዎች ከኣባልነትና ደጋፊነት ርቀዋል። ዶ/ር ብርሃኑና ዶ/ር ያዕቆብ ከቅንጅት ቢሰናበቱ የመርካቶ ነጋዴዎች ቅንጅትን መደገፍ ያቆማሉ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

# ሶ ስ ት

ስለኢትዮጵያ የፖለቲካ ዲስኩር ኦዴንስ ይህን ካልኩኝ ወደ ቅንጅት አመራር፣ አባላትና ደጋፊዎች ልመለስ። ከቅንጅት አመራርና የበላይ ተዋናዮች ልጀምር። በቅንጅት አመራርና የበላይ ተዋናዮች (ድጋፍ ሰጪዎች) በሁለት ልንከፍላቸው እንችላለን።

(1) የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስልጣንን (ዘውድን) ወደ ሸዋ ለመመለስ የሚታገሉ ብልጦች።

(2) በዘውግ ፖለቲካ ምክንያት ባልዋሉበት የጥፋተኝነት ስሜት (Guilty Conscious) የሚሰማቸው የዋሃን።

በተራ ቁጥር (2) የተካተቱት ዜጎች ቆም ብለው ምን እየሰሩ እንደሆነ ቢያስቡ፣ ያሳደጋቸው የአስተዳደርና የፖለቲካ ታሪክ ለተወሰኑ ደቂቃዎች እንኳን ለማስታወስና ለመገምገም ቢሞክሩ በተራ ቁጥር (1) ከሚመደቡት ፖለቲከኞች ጋር ማበር አልነበረባቸውም። ምናልባትም በዘውግ ፖለቲካ ላይ ያላቸው ቅዋሜ ይሄን የቤት ስራቸውን መስራት አላስቻላቸውም ይሆናል። አሊያም ቅንጅት የዘረኞች ሁሉ ዘረኞችና ወንዘኞች ስብስብ መሆኑን ቢያውቁም ከዚህ ሃይል ጋር ተጠግተን የተፈናጠረ ጥቅም እንለቃቅማለን ብለው የሚያስቡም ይመስለኛል። ለዚህም ነው የዋሃን ልላቸው የተገደድኩት። ልክ የበሬ "አካል" ካሁን አሁን ይወድቃል ብላ በሬውን ስትከተል እንደዋለች ቀበሮ።

በተራ ቁጥር (1) የመደብኩት ስብስቦች የፖለቲካና የአስተዳደር ብቃት በዘር የወረሱት ያህል የሚሰማቸው፣ ልካቸው እንኳን እስከምን እንደሆነ ቆም ብለው ለማሰብ ያልታደሉ፤ በትምክህት ያበዱ፣ የበላይነትና ስሜት የተጠናወታቸውና በዘረኝነት የሰከሩ ናቸው። እንደ KU KLUX KLAN።

ስለ ቅንጅት አመራርና የበላይ ተዋናዮች ይኸን ካልን፤ ደጋፊዎቻቸው ምን እንደሚመስሉ እንይ።

(1) የፖለቲካ ስልጣን (ዘውድ) ወደ ሸዋ ይመለሳል ከሚል ተስፋ የሚደግፉ።

(2) የቅንጅት አመራሮች የተማሩ በመሆናቸው የሚደግፉ።

(3) በቅንጅት ውስጥ ያለ የኛ ሰው ስልጣን ከያዘ እንጠቀማለን ከሚል የሚደግፉ።

(4) የዘውግ ፖለቲካ ስለማይወዱ (ስለማይመቻቸው) የሚደግፉ።

(1) የፖለቲካ ስልጣን (ዘውድ) ወደ ሸዋ ይመለሳል ከሚል ተስፋ የሚደግፉ።

በዚህ ቡዱን ውስጥ ያሉ ደጋፊዎች ምንም እንኳን ህልማቸው እውን የመሆኑ እድል የመነመነ ቢሆንም በዴሞክራሲ ስርዓትና ሂደት ውስጥ ለዚህ ዓላማ መታገል (በግልፅም በውጠታዋቂነትም) መብታቸው ነው። እንደነዚህ የመሰሉ ሃይሎች ባንድ ንቃተ ህሊናው የዳበር ወይም እየዳበረ በሚሄድ ማህበረሰብ ውስጥ እየከሰሙ የሚሄዱ ሃይሎች ናቸው። የኢትዮጵያ ምልዓተ ህዝብ ወደተሻለ የፖለቲካ ንቃተህሊና እስኪሸጋገር ድረስ እያጣጣሩ ይቆያሉ። እነዚህ የኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም ያገባናል የሚሉ ሃይሎች በጋራ ሊታገሉዋቸው ይገባል። ስለዚህ ቅንጅት ይህን የመሰለ ደጋፊ ይዞ እንደሙቀጫ ከመድበልበል አያልፍም።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

(2) የቅንጅት ኣመራሮች የተማሩ በመሆናቸው የሚደግፋ።

ከመዋእለ ህፃናት ትምህርት ቤት እስከ ዱክትርና መማር ብቻ ኣንድን ሰው ኣዋቂ ኣያደርግም። በዚህ ሂደት ውስጥ ኣከባቢን የምንገነዘብበትና የምተነትንበት እውቀት ማግኘት ኣለብን። የተለያዩ መፍትሂ የሚሹ ጉዳዮች (ችግሮች) በገጠሙን ቁጥር ለያንዳንዱ መፍትሂ የሚሻ ችግር ተገቢ መፍትሂ የመፈለግና የማግኘት ኣቅም ሲኖረን መማራችን ትርጉም ወይም ውጤት ይኖረዋል።

እዚህ ላይ በተጨባጭ ኣንዳንድ የኢትዮጵያ ግብርና ምሁራን ሲሳሳቱ በስእል (Scenario) ላመልክት። በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚከሰት ጉዳይ ነው። ወይም የዚሁ ተመሳሳይ ፍፃሜ ብዙ ጊዜ ይከሰታል።

*የግብርና ኣዋቂዎች የኣንድ መንደር (ጎጥ) ገበሬዎችን ስንዴ ሲዘሩ ዳፕ የተባላ ማዳበሪያ እንዲጠቀሙ ይመክሩዋቸዋል። ገበሬዎቹ ደግሞ "ከ5 ዓመት በፊት እንደዚሁ ማዳበሪያ ተጠቅመን ተቃጥሎብናል፤ ስለዚህ ኣያስፈልገንም" ይላሉ። የግብርና ምሁራኑ "ካቻምና ማዳበሪያ ተጠቅማቹ ማለፊያ ምርት ኣፍሳችሁ የለም እንዴ? የለም የለም መጠቀም ኣለባችሁ" ይሉዋቸዋል። ገበሬዎቹ ቀጠል ኣድርገው "ችግሩ ከመሬቱ ብቻም ኣይደለ፤ ከሰማዩም ጭምር ነው። ከ5 ዓመት በፊት የነበረው ሰማይና የዘንድሮው ተመሳስሎብናል። ያደግንበት ነው፣ እናውቀዋለን። የዘንድሮ ሰማይ ዝናብ የሚሰጥ ኣይመስለንም። ሰማዩ ሲለግም ደግማ ማዳበሪያው ማሳችንን ያቃጥልብናል። ስለዚህ ኣንፈልግም" ይላሉ። የግብርና ምሁራኑ እንደምንም ወትውተው ገበሬዎቹን ዳፕ እንዲጠቀሙ ያደርጉና ውጤቱ ገበሬዎቹ ያሉት ይሆናል።*

ለዚህ ነው መማር ማለት ለያንዳንዱ ችግር ተገቢ መፍትሂ ወይም ትንታኔ መሰጠት መቻል ነው የሚባለው። እላይ በምሳሌ ከተጠቀምኩባቸው የግብርና ባለሙያዎች ኣንዱ የቅንጅት ኣመራር ኣባል ቢሆን የተማረ ሰለሆነ የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ለመሆን ማለሙ ኣይቀርም።

የመማርና ማወቅ ልዩነት ሌላ ምሳሌ ላክል። ፖለቲካ። እዚህ ላይ እውነተኛ ሰዎች ብወስድ ጠቃሚ ይመስለኛል።

*ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ የኤክሰፐርት እውቀት (Expert Knowledge) ኣላቸው የምላቸው ሁለት ኢትዮጵያውያን ልውስድ፤ ክቡር ዶ/ር መራራ ጉዲናና ክቡር ኣቶ ተፈራ ዋልዋ። ዶ/ር መራራ የፖለቲካን ከንድፈሃሳብና ከሁለተኛ ደረጃ መረጃ (Secondary Data Source) በዙ ያውቃሉ። በተወሰነ ደረጃም በእንግዳ ተወናይነት (Guest Star) ያውቁታል። ኣቶ ተፈራ ደግሞ በንድፈ ሃሳብ፣ በተግባር ተዋናይ (Star) ሆነው፣ ከኢትዮጵያ ነባራዊና ታሪካዊ ሁኔታ ጋር በተሳሰረ መልኩ በነጠረ መልኩ ያውቁታል።*

በቅንጅት ገመድ ጎታች ደጋፊዎች ዘንድ ግን ኣቶ ተፈራ ኣያውቁም። መማርና ማወቅ ለየቅል ነው። የትግራይ ኣበዎች (እና እመዎች) "ካብያ ብኻፈር ምህሮስ ብኻፈር ኣእሙሮ" ይላሉ። ይህን



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ፅሁፍ በምፅፍበት ሰዓት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ለጀቸ ቪሊ የሰጡት ቃለ ምልልስ ኣዳምጥ ነበር። በኣፍሪካ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ምዕራባውያን የበኩላቸው ሚና እንዲያበረክቱ ሲማፀኑ ሰማኋቸው። ብቻየን፤

> *እኚህ ሰው ዴሞክራሲን እርሳቸው (እኔንም ጭምር) መቶ በመቶ ሊያረካ በሚችል መልኩ ኣላሰፈኑም እንጂ፤ ከሳቸው ጋር ኣሲምባ ተራራና በለሳ ወንዝ የነበሩ ጓዶቻቸው ደርግን የሚያህል ፀረ ዴሞክራሲ ሃይል ሲያስወግዱ ኣይተዋል። ይህን እንዴት እውን ሊሆን እንደቻለም ለመገነዘብ በሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ ነበሩ። በኣካዳሚክ ትምህርትም ጣራ የነኩ ሰው ናቸው። ይሁን እንጂ የኣፍሪቃም የኢትዮጵያንም የዴሞክራሲ ግንባታ እውን የሚሆነው በኣፍሪቃውያን ወይም በኢትዮጵያውያ ብቻ መሆኑን ኣሁንም ኣልተገለጠላቸውም። የሚቻለውንና የማይቻለውን፣ የሚሆውንና የማይሆነውን፣ የሚገባውንና የማይገባውን እንዲገለጥላቸው እንደ ኣዳም የሆነ እፅ የሚያበላቸው ሰው ቢገኝ።*

ነበር ያለኩት። ነገሩ "ካብያ ብኻፈር ምህሮስ ብኻፈር ኣእሙሮ" የሚለውን ኣባባል የሚያጠናክር ነው።

(3) በቅንጅት ያለው የኛ ሰው ስልጣን ከያዘ እንጠቀማለን ከሚል የሚደግፉ።

በዚህ ቡዱን ውስጥ ያሉት ደጋፊዎች ኣብዛኛዎቹ በኣሉታ የምመለከታቸው ኣይደሉም። ኣንድም የግል ጥቅም ፈላጊዎች ናቸው (ቁሳዊ፣ ስነልቡናዊ ወዘተ)። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያውያን የቆየ ባህሪይ ነው። ንቃተ ህሊናችን ሲዳብር የምንተወውና በዘላቂነት ኣደገኛ የማይባል ባህሪይ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ቡዱን ውስጥ ጥቂት ኣሳፋሪ ፍላጎት ያላቸው ኣሉ። የኛ ያሉዋቸው ሰዎች ስልጣን ሲይዙ፤ ግብር ሊቀነስላቸው፣ ጎረቤቶቻቸው ሲባረሩ ንብሮቶቻቸው በርካሽ ዋጋ ለመግዛት የሚያልሙ፣ ጓደኞቻቸው ከስራ ተባርረው እነሱ እንዲተኩ የሚያልሙ፣ ወንጀል ሰርተው ካገር የሸሹ ወደ ኣገርቤት ለመመለስ የሚሰልጉ፤ ወዘተ። ያም ሆነ ይህ በዚህ ቡዱን ውስጥ ያለ ደጋፊ ዘላቂም ኣይደለም ጠቃሚም ኣይደለም። ለተወሰነ ጊዜ ገመድ ያጓትታል።

(4) የዘውግ ፖለቲካ ስለማይወዱ (ስለማይመቻቸው) የሚደግፉ።

በዚህ ቡዱን ውስጥ የሚካተቱንም ህብረ በሄራዊ ፓርተ የሚሉትን መደገፍና ዘውግ ተኮር የሚሉትን ፓርት ኣለመደገፍ (መቃወም) ከማንም በላይ በቂ ምክንያት ኣላቸው ሊባሉ የሚችሉ ናቸው። ዘውግ ተኮር ፖለቲካና ጭፍን ዘረኝነትን ግን መለየት ኣለባቸው። ኣንደኛ የዘውግ ተኮር ፖለቲካ በራሱ የዘረኝነት ምንጭ ኣድረገው መቁጠር የለባቸውም። ምክንያቱም የኣብዛኛዎቹ የዘውግ ተኮር ፖለቲካ ተቀዋሚዎች የዘውግ ፖለቲካ ዘረኝነትን ያስፋፋል ብለው ያምናሉ። ሁለተኛ ህብረ በሄራዊ ፓርቲዎች የምንለው ቅንጅት በስም እንጂ ኣንድም ህብረ ብሄራዊ ኣይደለም፤ ሁለትም የለየለት የዘረኞችና የወንዘኞች መንጋ ስብስብ ነው። ስለዚ የዘውግ ተኮር የማይመቸው ሰው ከሁሉም በፊት መራቅ ያለበት ከቅንጅት ነው። በዚህ ቡዱን የሚካተቱ ደጋፊዎችም ሲውል ሲያድር ልብ የሚገዙ ናቸው። የቅንጅት ዓይነት ፓርቲ ዘላቂ ደጋፊዎች ሊሆኑ ኣይችሉም።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ከዚህ በላይ የቅንጅት ደጋፊዎች (እና የኢህአዴግ ተቀዋሚዎች) በምን ምክንያት ቅንጅትን እንደ ሚደግፉ በአጭሩ ለማመላከት ተሞክሯል። የተሰጡት ምክንያቶች ትክክል አይደሉም፤ እኔ ቅንጅትን የምደግፈው፥ በሚከተለው እንዲህ ዓይነቱ ኣገራዊ ርእዮተ ዓለም፣ በሚከተለው እንዲህ ዓይነቱ ኣገራዊ የፖለቲካ ኣቅጣጫ፣ በሚከተለው እንዲህ ዓይነቱ ኣገራዊ የኢኮኖሚ ስትራተጂ፣ በሚከተለው እንዲህ ዓይነቱ ኣገራዊ የጤና፣ የትምህርትና የማህበራዊ ጉዳይ ፖሊሲ፣ ባለው እንዲህ ዓይነቱ የፍትሃዊነትና የዴሞክራሲያዊነት ታሪክ (Track Record)፣ ወዘተ የሚለኝ ባገኝ ደስተኛ ነኝ። የት ይገኛል?

በወቅቱ በኣገራችን የተከሰተው የኑሩ ውድነት ችግር እንኳን፤ የኢህአዴግ የፖሊሲ ችግር ይሁን ኣይሁን፣ ለችግሩ መፍትሄ የተሻለ ስትራተጂ ይኑራቸው ኣይኑራቸው ኣልነገሩንም። ይልቁንስ መፍትሄ እንዲያመጣ ኢህአዴግን ሲማፀኑ ነው ያደመጥናቸው። የነጠረ ርእዮተ ዓለም ቢኖራቸው፣ የሚታወቅ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ኣቅጣጫ ቢኖራቸው ኣሁን ነበር ኢህአዴግን ወጥሮ መያዝ።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ምልኣተ ህዝብ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለመደገፍ ወይም ላለመደገፍ የሚያስችል ኣጠቃላይ ንቃተ ህሊናው የተገደበ ስለሆነ፤ ከላይ እንደተዘረዘረው ፓርቲዎች የፖለቲካ ፋይዳ በሌላቸው ባህሪዎቻቸው እንደ ዘር/ወንዝ፣ መልክ (Charisma)፣ የትምህርት ሰርተፊኬት፣ ኣፈጮሌነት ወዘተ ሲደገፉ እናያለን። የሚሳዝነው ደግሞ ፖለቲከኞቹም እነዚህ ባህሪዎቻቸው በማጉላት ህዝብን ከመሸወድ ውጭ የፖለቲካ ብቃትና ስልጡንነታቸው (Civility) ለማሳየት (ካለ) ጥረት ሲያደርጉ ኣናይም። በኢትዮጵያ ስኬታማ ፖለቲከኛ ለመሆን፤ ፕሮፌሰር መሆን፣ ዶክተር መሆን፣ መሃንዲስ መሆን፣ የህግ ምሁር መሆን፣ የምጣኔ ሃብት ጠቢብ መሆን፣ ወታደራዊ ጀግንነት ብቻ በቂ ኣይደለም። ይልቁንስ (1) የፖለቲካ ሳይንስ ማወቅን፣ (2) በፖለቲካ እንቅስቃሴ መፈተንንና ማለፍን፣ እንዲሁም (3) ኢትዮጵያን ማወቅ ይጠይቃል።

ደርግ/ኢሰፓ ሆነው የፖለቲካ ኣቀበት ያልወጡና የተፈረካከሱ የቅንጅት ካባ ለብሰው እንዴት ሊሳካላቸው ይችላል? ኢህኣፓ ሆነው ተሸንፈው የፈረጠጡ፣ ተንኮታኵተው የወደቁበትን ኣካሄድ ህይወት ለማዘራት እንዴት ይቃጣቸዋል? እነሱ የፈረጠጡበትን ትግል ዳር ካደረሱ ጓዶቻቸው ጋር ገመድ ለመጓተት እንዴትስ ወኔ ኣገኙ? ኣይ ዴሞክራሲ!



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com